የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ — ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 24
ADDIS ABABA – 14th May, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................ ገጽ ፻፸፬

## አዋጅ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፹፰

## ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፶፫ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

ከማናቸውም ገቢ ግብር ስለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፶፫ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሐ) ተተክቷል ፤

"ሐ) ማንኛውም ድርጅት በሚያገኘው ግብር በሚከፈልበት ገቢ ላይ ሰላሣ አምስት በመቶ (፴፭%) ግብር ይከፍላል ። ሆኖም በማዕድን ማምረት ሥራ የተሰማራ ድርጅት በሚያገኘው ገቢ ላይ ግብሩ የሚወሰነው ፤ የሚመደበውና የሚሰበሰበው በማዕድን ሥራዎች ገቢ ግብር አዋጅ መሠረት ነው ።"

፫· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## CONTENTS

Proclamation No. 36/1996
Income Tax (Amendment) Proclamation ... Page 174

## PROCLAMATION NO. 36/1996

## A PROCLAMATION TO AMEND THE INCOME TAX PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Income Tax Proclamation No. 173/1961;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Income Tax (Amendment) Proclamation No. 36/1996."

2. *Amendment*

   Sub–Article (c) of Article 12 of the Income Tax Proclamation No. 173/1961 (as amended) is hereby deleted and replaced by the following new sub–Article (c):

   "(c) Any organization shall pay thirty–five percent (35%) of income tax on its taxable income. However, tax on income from mining by an organization shall be charged, levied and collected in accordance with the Mining Income Tax Proclamation."

3. *Effective Date*

   This Proclamation shall come into force as of the 8th day of July, 1995.

Done at Addis Ababa, this 14th day of May, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001